# የጨገገው የትግል ስልት?

በድንበሩ ወሰኔ

ግንቦት 2004

ባለጌን ካሳደገ . . . ይሉ ነበር አበው ልጅን በመልካም ሥነምግባርና ጨዋነት አንፆ የማሳደግን አስፈላጊነት በአፅንኦት ሲገልፁ፡፡

መልካም ሥነ ምግባርና ጨዋነት የኢትዮጵያውያን አንዱ መታወቂያቸው በመሆኑ እኔ ከኢትዮጵያ ነኝ ብለን ራሳችንን ስናስተዋውቅ የሚቸረን በጎ ስሜትና ገፅታ የቱን ያህል እንደሆነ እናውቀዋለን፡፡ ይህ ካደግንበት ቤተሰብና ማህበረሰብ ያገኘነው መልካም ውርስና ትሩፋት በመሆኑ ደስ ይለናል፡፡

በረጅም ዘመን የድህነትና የኋላቀርነት ታሪካችን አንገታችንን የምንደፋውን ያህል እንዲህ ዓይነት እሴቶቻችን ደግሞ የሚያኮሩን ናቸውና የሚያሳንሰንን ድህነትና ኋላቀርነት ከላያችን ላይ ለመጣል የምንታገለውን ያህል በጎ በጎ የሆኑ እሴቶቻችንም ለመጠበቅና ለልጅ ልጅም ለማቆዬት የዛኑ ያህል መትጋት ይገባናል፡፡

መልካም መገለጫዎቻችንን መጠበቅም ሆነ ማበላሸት በሁላችንም የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴና ተግባር ተፅዕኖ ሥር የሚሆን ጉዳይ ነውና በየዕለቱ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የምንፈፅማቸው ተግባራት በዚህ ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡

የዚህች ፅሑፌ አነሳስም በቅርቡ በዚህ በዋሽንግተን ጀግና እዬተባለ ሙገሳና ውዳሴ የተቸረው የሰሞኑ ጀብደኛ የስነ ምግባር ጉድለት የእኛ የኢትዮጵያውያንን የመልካም ሥነምግባርና ጨዋነት ገፅታችንን በእጅጉ ያጎደፈ በመሆኑ በግል ተሰማኝን ቅሬታና ትዝብቴን ፈንጠቅ ማድረግ ነው፡፡

ድርጊቱ እኔን ብቻ ሳይሆን ብዙዎቻችሁንም ያሳዘነና ያሳፈረ የመሆኑን ያህል አንዳንዶችን ደግሞ ሲያስፈነጥዝና ሲያስቦርቅ ተመለከትንና ጉድ፣ ብለን ከቀደመው በላይ አዘንን አፈርንም፡፡

“ጀግና የጀግና ገድል” እየተባለ ሊወደስ የተሞከረው ይኸ ጉዳይ መቼም ሁላችንም እንደሰማነው ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ርካሽ ተግባር ምን የሚሉት ነው? ብለን ንቀን ልንረሳው ስንሞክር አሳፋሪ ድርጊቱን ሊያወድሱና ሊያሞካሹ የሚሞክሩ ብቅ ብቅ ማለታቸውን ስናይ “የባሰ አለ . . . ” አሰኘን፡፡

እርግጥ ነው በድርጊቱ ሊፈጠርብን የሚችለው ስሜት እንደየማንነትና የመረዳት ልካችን የሚለያይ ስለሚሆን ብዙዎቻችን አዝነናል አንዳንዶች ደግሞ ጮቤ ሲረግጡ አምሳያቸውንም ሲያደንቁ ተስተውሏል፡፡ ምንም ቢሆን ግን ምንም ያህል ማር መሳይ ቀባብተን ልናጣፍጠው ብንሞክር ከቶም ሊጥም የማይችል አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሙከራውም በአእምሮአችን ይዘት ላይ ትዝብትን የሚፈጥር ነው፡፡

በአፍሪካ አህጉር የሚሊዮኖች የህልውና ጉዳይ በሆነው ግብርናና የምግብ ዋስትና ላይ ለመምከር ከየአቅጣጫው የመጡ የየሀገራት መሪዎች፣ ምሁራን እና ሌሎችም የሚገባቸው ሁሉ በተሰበሰቡበት አዳራሽ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የጋዜጠኝነት ተግባሩን ለማከናወን አስፈቅዶ ለዚሁ ተግባር ብቻም ተፈቅዶለት ከአዳራሹ የዘለቀው ጋዜጠኛ ጥቂት እንደተቀመጠ በምክንያታዊነት ሳይሆን በስሜት ፈንድቶ ቀበጣጠረ አምቧረቀ፤ ጉባኤውን ሊያውክ ሞከረ፡፡

የተቃውሞ ፖለቲካ መሆኑ ነው፡፡ አዎ ድምፁን ከፍ አድርጎ ልቡን ነካ እንዳደረገው ሲያምቧርቅና የሚጥል በሽታው እንደተነሳበት ሲንደፋደፍ የተሰብሳቢው ሁሉ ቀልብ ወደ ድምፁ ተስቧል፡፡

ኋላ ሁሉም ነገሩ ገባው፡፡ አንዱ ታዲያ እንዲህ ከሆነ በቦታው ቢያደርገው አይሻልም ነበር እኛ ሰልፈኞች አይደለን? እያለ ሲጠይቅ ሌላው ደግሞ እንዲያ መስሎት ቢሆን ነው እንጅ አረ እንዲያውም ድምፁን አሰምቶ ዙሪያ ገባውን እየተመለከተ ተቀብለን እንድንደግምለትም እየጠበቀ ነበር መሰለኝ ብሎ ጓደኛውን ፈገግ እንዳደረገው አንድ ፀሐፊ አስነብቦናል፡፡

ብቻ ብዙ እድል አልተሰጠውም እንጅ ቢሰጠው ጥሩ ነበር ነገር ግን ተሰብሳቢዎቹ እንዲህ የጨዋታ ጊዜ በፕሮግራማቸው አልነበራቸውምና አፉ ላይ እንኳ የጀመረውን ሳይስጨርሱት በደህንነት ሰራተኞ እያከታለቡ አስወጡት፡፡

ሰውየው አንቱ የተባለ፣ የምንትስ ሽልማት ተሸላሚ . . . ስለነበር ሙያዊ ኃላፊነቱን ይወጣል ተብሎ ፈቃድ አግኝቶ በክብር በአዳራሹ ተቀምጦ እንዲሳተፍ ተፈቀደለት የገባ ቢሆንም ነገር ግን በክብር የተጠራበትን ትቶ አስቦ፣ ጭምብል ለብሶ፣ ተዘጋጅቶ፣ ከአማካሪዎቹም ጋር ብዙ በምክክር ብዙ ጊዜ አጥፍቶ በመድረኩ ሊያቀርበው የሞከረውን መነባንብ ይሁን ጭውውት በቅጡ ሳይጫወተው ስብሰባውን አታውክ ተብሎ አዳራሹን ለቆ እንዲወጣ ተደረገ፡፡

በትክክል የሆነውና በሰውዬውም አንደበት የተረጋገጠው የታሪኩ ጭብጥ መጀመሪያም መጨረሻም ይኸው ነው፡፡

ሁሌም ሰው በሚገባው ቦታና ሁኔታ በአግባቡ ሲገባና ሲገኝ ያምርበታል ስራውም ይሳካለታል፡፡ ያ ሳይሆን ሲቀር ግን ኪሳራ ነው፡፡

ጋዜጠኛ መቅረፀ ድምፁን ጥሎ በድፍረት ቤተ መቅደስ ገብቼ ልቀድስ ብሎ ቢነሳ ያለስገባው ገብቷልና ምዕመኑን በማሳዘኑ ውግዘትና ውርደት የሚደርስበት ከመሆኑም በላይ የመውጊያውንም ብረት ተቃውሟልና ይዋል ይደር እንጅ የመርገምትና ቅስፈት ፍሬን ማጨዱ አይቀርም፡፡

መቃወምና የተቃውሞ ድምፅን ማሰማት በእኛ በምድራውያኑ ብቻ ሳይሆን በፈጣሪም ዘንድ የተከለከለ አይደለምና ተቃዋሚ መሆን ያለ የነበረ ወደፊትም የሚኖር ነው፡፡ እናም ሰውየው በሥልጣን ላይ ያለው መንግስት ተቃዋሚ ሆኖ ይህንኑ የፖለቲካ አስተሳሰቡን የማራመድ ሙከራ ሆኖ ይህም በአግባቡ ተፈፅሞ ቢሆን እኛም ይህንኑ ልናይ እንችል ነበር፡፡

እዚህ አሜሪካን እየኖረ ለሚያይ፣ ለሚያነብና ለሚፅፍ የዓለም ጋዜጠኞች ማህበር አባል ለሆነ ለዚያውም ለዶሞክራሲያዊ መብት ተሟጋች የፖለቲካ ተቃውሞን የማሰሚያ መንገዱን እንዴት ያጣዋል ብለን እናስብ? አይጠፋውም ካልን ደግሞ እንዲህ በሰለጠነ ሀገር የሚኖር ስልጡን እንዴት እንዲህ በአደባባይ  የጋጠወጥነት ባህሪውን ይዞ ይወጣል?

አንዳንዴ በቅጡ ሳይታሰብበት በስሜት ጡዘት ብቻ  የሚፈፀም ድርጊት ምንም ፋይዳ ላይኖረው ሰሚና ተመልካችን የሚያሳዝንና የአድራጊውንም የአእምሮ ጓዳን ወለል አድርጎ የሚያሳይ ሆኖ ያልፋል::

በእጅጉ የሚያስገርመው ደግሞ ይኸ የመሰሎቹና የአድናቂዎቹ ባዶ አድናቆትና ቀፎነት ነው:: ለነገሩ የጠራ የፖለቲካ አጀንዳና የትግል ስልት የሌለው ቡድን እና አባላቶቹ እንዲህ ዓይነት ጀብደኞችን እያሰማራ ዓላማ ማሳካት ባይችሉም መወራጨት መቻላቸውንም ቢሆን ድል አድርጎት ድምፁን ከፍ አድርጎ ጉሮወሸባዬ እያለ ሊያቅራራ ቢሞክር ሊታዘንለት እንጅ ሊፈረድበት አይገባም:: የማታገያ ስልቱ ስለሆነ::

የአድናቂዎቹ የአድናቆት አገላለፅ አስገራሚም አስቂኝም ነው:: አንዱ ያለ ምንም ሐፍረት ከአፄ ዮሐንስ፣ ሌላው ከነ አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስገዶም፣ ሌላው ከዘርዓይ ደረስ፣ አንደኛው ደግሞ ከአበበ ቢቂላ ጋር ሲያመሳስለው ተመለከትን:: ይኸ የኋለኛ እንኳን የግብርም ባይሆን የስም መመሳሰል ስላገኘ የማመሳሰል ችሎታው የተሻለ ነው ተሳክቶለታል ሊባል ይችላል:: ሌሎቻችሁ ግን በእውነት እነዚህ የጠራችሁዋቸውን ስሞችና ታሪካቸውን ታውቁታላችሁ?

ወይ ጉድ እንዴት ይገርማል?

ሰው አንብቦ፣ ጠይቆ፣ ጠንቅቆ ባልተረዳው ጆሮ ጠገብ በሆነ እውቀትና ስሜቱ ብቻ እየተነዳ ሳያውቀው ያወቀ የመሰለውን ቁንፅል ነገር ይዞ እያጣቀሰ አንዱን ያለግብሩ ሊያሞካሽና ሊክብ ሲሞክር የነዚህን ድንቅ ባለታሪኮች በወርቅ ቀለም የተከተበ ታሪክ እያሳነሰና እያቆሸሸ መሆኑ ይታሰበው ይሆን?

ይኸ ትልቅ ታሪክን ማጉደፍ የዚያ ታሪክ አካል የነበረውንና የዚህን ትውልድም ማሳዘን መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል::

እርግጥ ነው ሁሉም የስኬት ባለቤት ሆኖ ሥራው ስሙን ከፍ ቢያደርገው መልካም ነው:: ሰው በህይወት ዘመኑ ባከናወነው ልዩ ጠቃሚ ተግባር ብቻ ሳይሆን መልካም ሥነ ምግባሩም በቀብር ሥነ ሥርዓታቱ ላይ ሲነብብ ሲሰማም ደስ ይላል:: እናም ሰው በበጎ ምግባሩ ቢወደስ ክፋት አልነበረውም አድናቆት ያለቦታው ሲመጣ ግን በተቃራኒው ያለውን ጉድለት ተመለከቱ እንደማለት ነው::

ባነሳነው ጉዳይ የአድናቆቱ ሌላው መነሻ የሚመስለኝ አሰላለፋችንን ባደረግንበት ጎራ ለአመታት ያለመሰልቸት ሆኖ ለማዬት የምንፈልገው ሳይሆን መና ሆኖ ይቀርና  ስሜታችንን ድብን ሲል እዚህ ግባ ለማይባለው  ትርጉም ሰጥተን ስሜታችንን  በመሸንገልና በመደለል ራሳችንን ለማፅናናት ከመፈለግ ነው::

አዎ ጠብ የሚል ነገር ሳይታይ ዓመታት ሲነጉዱ ዕድሜ እያለቀ ሲመጣ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች እየተላኩ ወደ ኋላ ዞረው ድንጋይ ወርውረው ሲመለሱ ጉሮ ወሸባየ . . . ጀግና ድል አድርጎ ሲገባ . . . እያልን እተጫወትን መኖራችንን ካላወጅንማ ምኑን አለነው? ቢያንስ ህልውናችንን ካላረጋገጠልን ደግሞ ትግል ያስጠላል።

ተደጋግሞ እንደሚመከረው አንድ ሰው ወይም ቡድን ለአንድ ነገር ሲነሳ ይዞት የተነሳው ጉዳይና መንገድ ትርጉም ያለው ርቀት ሊያስኬደው ይችል እንደሆነ በቅድሚያ ማረጋገጥ ያስፈልገዋል። በሂደትም ጉዞውን እፈተሸ ተገቢውን ማስተካከያ እያደረገ በጥንቃቄ መራመድ ይኖርበታል።

ይህ ካልሆነ በሀምሳም በመቶም አመታት ወደሚፈለገው ግብ መቅረብ አይቻልም። ይህ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ እንዲህ እንቶፈንቶ ወደሆኑ ተግባራት ሽግግር ማድረግ ይመጣል የቁልቁለት መንገድ ጉዞ ያስጀምራል። አስተውሎ የሚራመድ ብዙ ርቀት ይጓዛልና።

በተቃውሞው ጎራ ዛሬም ሊጠራ ያልቻለው ችግር ይኸ ነው። መንገድም፣ መሪም ተመሪም ስለሌለ አንድም እርምጃ ወደፊት መራመድ አልተቻለም። ላለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት የተሳካ አንድ ነገር ብቻ አይተናል። ያለውን እንደሌለ፣ የተሰራውን እንዳልተሰራ፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ ወዘተ እያደረጉ በመቃወም መኖርን ለማረጋገጥና ተስፋ የሌለው የጨገገ የትግል ስልት እያራመዱ መወራጨት።

የፖለቲካ ትግል በስሜት ብቻ የሚጋለብ ነጭ ፈረስ ሳይሆን ከስሜት በላይ የሀገርና የህዝብን ጥቅምና ፍላጎት በማስቀደም በብስለትና በጥንቃቄ በተነደፈ ፕሮግራምና መርህ ላይ የሚመሰረት ነው። በስሜት ሆያሆዬ መጫወት ይቻል ይሆናል ነገር ግን ሀገር መገንባት አይቻልም። ህዝብን አስተባብሮ መምራትና ሀገር መገንባት ከደመነፍስ ማላዘን በጣም የራቀ ጉዳይ ነው።

በተለያዩ ጊዜያትም እናውቃለን ብለው ህዝብን ከጎናቸው ለማሰለፍ ተነስተው የነበሩ ነገር ግን ጥቂት መራመድ ሳይችሉ በበየስርቻው ተሰነካክለው የቀሩት ይህንኑ በቅጡ ማጤን የተሳናቸው ናቸው። ግልፅ ራዕይና የፖለቲካ ፕሮግራም ያላቸውማ በበየትግል መስኩ የታዛቢን ቀልብ የሚስብ አለምን የሚያስደምም ውጤት ሲያስመዘግቡና ከድል ወደ ድል ሲሸጋገሩ በዕድሜያችን አይተናል።

የተረገመ ልጅ ያባቱን ሐውልት ያፈርሳል እንዲሉ ለበጎ ነገር እና ለውጤት ያልታደለው ግን ሁሌ የተሰራውን ለማፍረስ ሲፍጨረጨር ዕድሜውን ያገባድዳል። መስራት የማይችል ስለምን በበጎ ስራው በምሳሌነት የሚጠቀስን ይቃወማል? ህሊና ክፉና ደጉን እንድናውቅ የተሰጠን በመሆኑ ያልተገባ ነገር ስናስብ ወይም ስንሰራ ህሊናችንም እኮ ይወቅሰናል።

ለማፍረስ ሳይሆን ለመስራት ለመገንባት እንተባበር። ተባብረን ከሰራን ደግሞ ጥሩ ህይወት ኖረን በጥሩ ሥራ ጥሩ ሀገር ገንብተን ለትውልድ የተሻለ ነገር ጥለን ማለፍ እንችላለን። እያንዳንዳችን የየድርሻችንን ገንቢ አስተዋፅኦ ብናበረክት የጋራ ሀገራችንን የተሻለች ልናደርጋት ይቻለናል።

ይህ ካልሆነልን ደግሞ ከመንገድ ላይ ዞር በማለት እንቅፋት ከመሆን መቆጠብም ትልቅ አስተዋፅኦ ነው፡፡

ለጋዜጠኛው አበበና አድናቂዎቹ ሁሉ እስቲ አንድ  ምክሬን ልለግስና የዛሬውን ላብቃ፡፡ እስቲ ቆም እያልን በማሰብና በማስተወል እንራመድ፡፡ ከተራ የስሜት እብጠቶችና ትኩሳቶች ወጥተን ይህች ሀገር እያስመዘገበችው ባለው አበበና ባልንጀሮቹም እንደሰማችሁት በዚያን ዕለቱም ስብሰባ በተደጋጋሚ በአርአያነትም ከማንም ቀድማ እየተጠራችበት ለለው ለተያያዘችው የዕድገት ጉዞ አንድ ጠጠር እንጣል፡፡ ከቀን ቅዠትና ከባዶ ጩኸት ተላቀን አንድ ሻማን በማብራት ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር የዚህ ታሪካዊ የህዳሴ ጉዞ አካል እንሁን፡፡

ቀሺም የሆነው የቀሽም ነውና እንተወው፡፡ ለመልካም ነገር እንትጋ፡፡ በጤናማና በሰከነ አእምሮ ቆም ብለን እያስብን፣ በማስተዋል እየተራመድን የሚደገፈውን እንደግፍ፣ የሚደነቀውን እናድንቅ፣መቃወም ያለብንን እንቃወም የሚወገዘውንም እናውግዝ፡፡

ከመሸበት የፖለቲካ ሽኩቻ ተላቅቀን ከረጅም ዘመን መኻታ በኋላ በዕድገት ጉዞ ቆማ ለመሄድ በመውተርተር ያለች ሀገራችንን በእውነተኛ የልጅነት መንፈስ እየደገፍን አይዞሽ ልንላት እንጅ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለቸው እንሰሳ እያሰብን በጭካኔ ቁልቁል ልንገፈትራትና በነበረችበት ጥልቅ ጉድጓድ ልናቆያት አይገባም፡፡

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ገብቶንም ይሁን ሳይገባን ለእናታችን የቤት ውስጥ የልጅ ጠላት ሆነን የጠባናቸው ጡቶቿን ለመንከስ የምንታትር ሁሉ ቆም ብለን እናስብ፡፡

ቅን ልቦናውን ያድለን፡፡፡